# የሙት ሂስና የሃያስያኑ ትስስር

**ዮናስ** 01/29/14

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት ጋር በመሆን በነፃ ፕሬስ ስም በህግ ተመዝግበው በመፅሄት ህትመት ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችን (መፅሄቶችን) የተመለከተ ጥናት አድርገዋል፡፡ የጥናቱ ውጤትም ‹‹በኢትዮጵያ ከሚታተሙት መፅሄቶች መካከል ሰባቱ ማለትም አዲስ ጉዳይ፣ ፋክት፣ ሎሚ፣ ቆንጆ ጃኖ እንቁና ሊያ የተባሉት በብዙ ባህሪያቸው የፅንፈኛ ፖለቲካ ፓርቲ ልሣን መሆናቸውንና በተሳሳቱ መረጃዎችና ይዘት ህዝቡ በሥርዓቱ ላይ እምነት አጥቶ ለአመፅ እንዲነሳሳ የሚያደርጉ ዘገባዎች ያቀርባሉ›› የሚል ነው፡፡ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ረቡዕ ታህሳስ 30 ቀን 2006 ባወጣው ዐቢይ ዜና ላይ ማስነበቡን ተከትሎ የተለያዩ የህትመት ውጤቶች በተለይም የጥናቱ ውጤት መገለጫቸው ነው የተባሉት መፅሄቶች በጉዳዩ ላይ ብዙ እያሉና ሰፊ ሽፋንም እየሰጡት ነው፡፡

መፅሄቶቹ የተፈተሹበትን የይዘት መረጃዎች ከተመለከቱት ስድስት መመዘኛዎች ውስጥ በተለይ ‹‹የኢኮኖሚ እድገቱን የሚክዱ›› በሚል የቀረበው መመዘኛ ላይ እኔም በግል አልስማማም፡፡ ከመስከረም 1 ቀን 2006 እስከ ህዳር 30 ቀን 2006 የታተሙት ከላይ የተጠቀሱት መፅሄቶች የተቀሩት አምስት መመዘኛዎች (የመንግሥት ኃላፊዎችን የግል ስብዕና የሚነኩ፣ የአመጽ ጥሪዎችን የሚጠሩ፣ ሽብርተኝነትን የሚያበረታቱ፣ የፖለቲካ ሥርዓቱን የሚያጨልሙ እና ህገ መንግሥቱን የሚያጣጥሉ) የሚገለጹ መሆናቸው ላይ ድብን አድርጌ ስለመስማማቴ አብነቶች እያነሳሁ እሞግታለሁ። ይህ ሙግት ግን የዚህ መጣጥፍ ሁለተኛ አጀንዳዬ ነው፡፡ ዋናውና ዐቢይ ጉዳዬ ጥናቱን ተከትሎ በመጽሄቶቹ የቀረቡት ሂሶች ናቸው፡፡ እነዚህ ሂሶች ጥናቱን ወደ ጎን ገፍተው አጥኚዎቹን፣ ጥናቱ ላይ በመንግሥት ሚዲያ የተሰጡ ሀሳቦችን ትተው ሀሳብ ሰንዛሪዎቹ ላይ ትኩረት ያደረጉ በመሆናቸው ለእኔ የሙት ሂስ ጥሩ መገለጫ ሆነውኛል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ሙት ሂሶች ጥናቱን ትተው አጥኚው ላይ፤ ሀሳቡን ትተው ሀሳብ ሰንዛሪው ላይ ባደረጉት ርብርብ የፖለቲካ ሥርዓቱን አጨላሚ፣ ህገ መንግሥቱን አጣጣይ፣ የመንግሥት ኃላፊዎችን የግል

ስብዕና ነኪ፣ የአመጽ ጥሪዎችን አስተላላፊ፣ ሽብርተኝነትን አበረታች መሆናቸውን ማረጋገጣቸው አጽንኦት ሊሰጠው የሚገባ ነጥብ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

ጥናቱን ትተው አጥኚው ላይ፣ ሀሳቡን ትተው ሀሳብ ሰንዛሪው ላይ የተደረጉ ዘመቻዎችን ጥናቱ ከሚመለከታቸው መጽሄቶች በአንደኛ ደረጃ ከሰፈረው አዲስ ጉዳይ ማሳያዎችን ወስደን የሙት ሂስ ጥሩ መገለጫ ስለመሆናቸው ካረጋገጥን በኋላ የጥናቱ ይዘት መለኪያን መሠረት በማድረግ በእርግጥም እስማማባቸዋለሁ ባልኳቸው አምስት ነጥቦች መጽሄቶቹ የሚገለጹ ስለመሆናቸው ማሳያ የሚሆኑ ነጥቦችን በተለይ ከፋክትና አዲስ ጉዳይ፣ መጽሄቶች የተወሰኑ ህትመቶች ላይ በማንሳት ሙግቴን እቋጫለሁ፡፡

አዲስ ጉዳይ መጽሄት በ‹‹ማንን እንማ›› ገጹ የጥናቱን ይዘት ትቶ ከላይ የተመለከቱትን አጥኚ ተቋሞች ‹‹አዲሶቹን ፍርድ ቤቶች›› በሚል ርዕሱ ኩርኩማውን የጀመረ ሲሆን የጥናቱን ይዘት የተመለከተ አንዳች መሟገቻ ሀሳብ ሳይሰነዝር የአጥኚዎቹን ግለሳባዊ ማንነት ከእውቀት ከልምድና መሰል ቁመናቸው አንጻር ‹‹ከእውቀት ነጻ›› በሆኑ ሰዎች የተሰራ ‹‹ጥናት ተብዬ ነገር›› በማለት አንደኛውን ዘመቻ ይቋጫል፡፡

ሌላውና በዚሁ ገጽ በሌላ ርዕስ የሰፈረ ይዘቱን የዘነጋው ሙት ሂስ መጽሄቶቹ ‹‹የቀለም አብዮት ያስተናገዱ አገሮችን ቅኝት የሚከተሉ ሆነው ይታያሉ›› የሚለውን ከጥናቱ የተወሰደ ነጥብ መሠረት በማድረግ የተሰነዘረ ነው፡፡ ‹‹ምርጫ ከመቃረቡ በፊት የገዢው ፓርቲ ሊወስዳቸው የሚፈልጋቸው እርምጃዎችን የሚያሳብቅ ነው›› የሚለው ነጥብ ከአጥኚ ተቋማቱም የዘለለ እና የማይገኛኝ አካል ላይ የተወረወረው ጠጠር ነው፡፡

የአዲስ ጉዳይ መጽሄት የሙት ሂሶች መገለጫ የሆነውና በእርግጥም የሙት ሂሶች ሁሉ ራስ የሆነው ሙት ሂስ የሰፈረው ደግሞ በማስታወሻ ፖለቲካ ገጽ ላይ ነው፡፡ ይኸውም የ‹‹አዲስ ዘመን አሮጌ ወሬዎች››! (ንኩ-ጋዜጣና ንኮቹ- ጋዜጠኞች) በማለት ጥናቱን በመተው አጥኚ ተቋማቱንና ጥናቱን በተመለከተ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የህትመት ዳሰሳ ፕሮግራም ላይ በተጋባዥነት ቀርበው አስተያየት የሰጡ ጋዜጠኞች ላይ የተሰነዘረው ሙት ሂስ ነው፡፡

ቅዳሜ ጥር 3 ቀን 2006 በነበረው የህትመት ዳሰሳ ላይ ተጋብዘው ጥናቱን የተመለከተ ሀሳብ የሰነዘሩት የሰንደቅ ጋዜጣ ምክትል ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ፋኑኤል ክንፉ እና ለድረ ገፅ የሚፅፈው ጦማሪ (bloger) ዳንኤል ብርሃኔ ናቸው፡፡ ታዲያ ሙት የሆኑት ሃያሲና

ሂሳቸው እነዚህ ግለሰቦች ጋዜጠኛ መሆናቸውንም ባለመቀበል በትምህርተ ጥቅስ በማመላከት የጀመረ ሲሆን የሂሱና የሃያሲው ሙትነት የሚከፋው ደግሞ አስተያየት ሰጪዎቹ የሰነዘሩትን አስተያየትና ሃሳብ ማብላላቱ ቀርቶ ለአንባቢያን ለማስታወስ እንኳ ሳይፈቅድ በቀጥታ የግለሰቦቹን ማንነት ማጠልሸቱ ነው፡፡

ይህ ሙት ሂስና ሙት ሃያሲ ሰለሞን ተሰማ ጂ የተባለ ሰው ሲሆን ሙት ሂሶቹን የማውቀው በዚህ ብቻ ሳይሆን በሌላም አጋጣሚ በመሆኑ ለእኔ አልገረመኝም፡፡ ይኸውም በረከት በላይነህ በተባለ ጋዜጠኛ ገጣሚና ተዋናይ ተደርሶ ለንባብ የበቃውን ‹‹የመንፈስ ከፍታ›› የተሰኘ የግጥም መድብል ሳያነብ የሰጠው ሂስ ሙት ስለመሆኑ በተግባር በመረጋገጡ የደረሰበትን ውርጅብኝ በሌባ አይነደረቅ…መንገድ ለመመከት የሞከረበት ሙት መጣጥፍ ነው፡፡

የአዲስ ጉዳይ ሙት ሂሶች በዋናነት ከተሰነዘሩበት ሌላውና ሰፊው ደግሞ በዐቢይ ጉዳይዋ ላይ የተዘረዘረው ነው፡፡ ጥናቱንና የጥናቱን መነሻና መድረሻ በዝርዝር ያልቃኘው ይህ ሙት ሂስ ጥናቱን ከምርጫ ጋር በማያያዝ ለሙት ሂሱ ‹‹ምርጫ መጣ ፕሬስ ውጣ!›› የሚል ርዕስ የሰጠው ግልብ ትርክቱ ‹‹የምርጫ መንገድ ማፅጃ›› ‹‹ኢ-ሣይንሳዊ ጥናት ለፖለቲካ መሳሪያነት››፣ ‹‹የፖለቲካ ቁርሾ ወይም የቂም እሹሩሩ›› ህገ ወጥ ጥናትና መሰል ትርጉም ያላቸውን ታፔላዎች ለጥናቱ በሙት ሂሱ ለጥፏል፡፡ ይህንን ሙት ሃሳብም የመፅሄቱ አቋም በሚገለፅበት ርዕሰ አንቀፅ ጭምር ‹‹ ከመጠምጠም ማወቅ ይቅደም›› በማለት ዘልፎ ተቋማቱንና በጥናቱ ስማቸው እንኳን ያልተገለፁትን አጥኚዎች ‹‹አላዋቂ›› በማለት ዘልፎ ሲያበቃ ራሱን ሰማይ ላይ በመስቀል ‹‹የአዋቂነቱን›› ጥግ ለማሳየት ደፍሯል፡፡

አሁን አነዚህን ሙት ሂሶች ይዘን በእርግጥም በጥናቱ የተመለከቱት አምስት ነጥቦች እነ አዲስ ጉዳይ እንደሚገለፁ የሚያረጋግጡ ጭብጦችን በተለያየ ጊዜ ታትመው ለንባብ ከበቁት መፅሄቶች እየመዘዝን በመመልከት በ‹‹ከመጠምጠም ማወቅ ይቀድም›› የአዲስ ጉዳይ ሙት ሂስ የሰፈሩ አዲስ ጉዳይ የተኮፈሰባቸው ነጥቦች ግልባጩን መሆኑን በማሳየት ትርክቴን እደመድማለሁ፡፡

ከቁጥር 181 መስከረም 4 ቀን 2006 የአዲስ ጉዳይ መፅሄት ስንጀምር መፅሄቷ በሰሞንኛ ጉዳይ አምዷ የመንግሥት ባለሥልጣናትን የግል ስብዕና ያንኳሰሰችበትንና ህገ መንግሥቱን ያጣጣለችበትን አጀንዳ እናገኛለን፡፡

‹‹ኢህአዴግ ቀጣዩን የሀገሪቱን ፕሬዚዳንት እያዘጋጀ ነው›› በሚል ርዕስ ለንባብ የበቃው ይህ ፅሁፍ የሀገሪቱን ያሉና የነበሩ እንዲሁም ወደፊት የሚሾሙ ፕሬዚዳንቶች ‹‹ጥርስ ለሌለው ሹመት ጥርስ የሌለው ተሿሚ›› የሚልና ‹‹የማይቆረቁር ታማኝና ታዛዥ ፕሬዚዳንት›› በማለት ይልቁንም የቀድሞውን ፕሬዚዳንት ግርማ ወልደጊዮርጊስ በፎቶ አስደግፎ ጭምር የተሳለቀባቸው ሲሆን በአጋጣሚውም የሀገሪቱን ፕሬዚንዳንት ተግባርና ኃላፊነት የሚወስነውን ህገ መንግሥት ለግለሰቦች ማንኳሰሻ መነሻ በማድግ አጣጥሎታል፡፡ ስለሆነም በዚህችውና ከመፅሄቱም አንዷ በሆነችው አጀንዳ ላይ ብቻ ሰሞነኛ በሆነው ጥናት ላይ አዲስ ጉዳይ ከተመዘነችባቸውና እኔም ከተስማማሁባቸው አምስት ነጥቦች በሁለቱ ‹‹የመንግሥት ባለሥልጣናትን በማንኳሰስና ህገ መንግሥቱን በማጣጣል›› መገለፁን ልብ ይሏል፡፡

ከላይ በተመለከተው ቀን ለንባብ በበቃችው መፅሄት ዳግም የጥናቱን ሁለት መመዘኛዎች አሟልታ የምትገኘው ደግሞ በወቅታዊ ጉዳይ ገፅ ላይ ባሰፈረችው ‹‹በመለስ ራዕይ የተሸፈነው የመለስ ሌላ ስብዕና›› በሚለው ፅሁፍ ነው፡፡ በዚህም ቢሆን እንኳን ‹‹ሟች አይወቀስም›› በሚባልበት ሀገር ላይ የቀድሞውን ጠቅላይ ሚኒስትር በማሳነስና በማንኳሰስ በመለስ ራዕይ አቋራጭ ፖለቲካዊ ሥርዓቱን የሚያጨልሙ እና የሚያጠልሹ ትርክቶችን አስነብባናለች፡፡

አሁንም በዚህኛውና ከላይ በተጠቀሰው ቀን ለንባብ በበቃችው መጽሄት ‹‹ኢትዮጵያ በአዲሱ ዓመት ምኞትና ተስፋ›› በሚል ርዕስ ስር የፅንፈኛ ፖለቲካ ፓርቲዎችን አመራር በመጋበዝ ‹‹ህዝቡ በሥርዓቱ ላይ እምነት እንዲያጣ የሚያደርጉና አመፅ የሚቀሰቅሱ›› ጥሪዎችን በአመራሮቹ በኩል አስተናግዳለች፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ይህችው መፅሄት በዚሁ ህትመቷ ‹‹የፖለቲካ ለውጥ ያስፈልገናል›› ባለችበት ዐቢይ ጉዳይዋ ‹‹ሃገራችን ያለችበት ሁኔታ በእጅጉ አሳሳቢ እንደሆነ ይሰማኛል›› በሚል ርዕስ በነፃ መድረኳ ያሰፈረቻቸው ትርክቶች ህዝቡ በሥርዓቱ ላይ ተስፋ እንዲያጣ፣ መንግሥትን እንዳያምንና በህገ ወጥ አግባብና ህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በተፃረረ

መልኩ ለውጥ ለማምጣት የሚረዱ የአመፃ ጥሪዎችን ያስተናገደችባቸውን ፅሁፎች ስንመለከት በእርግጥም ከዚህ በላይ የቀለም አብዮትን ቅኝት የተከተለ ዘገባ ከወዴት ይገኛል ያስብላል፡፡ እንግዲህ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር በአንዲት  ህትመት ላይ ከተስማማሁባቸው አምስት መመዘኛዎች አዲስ ጉዳይ በአራቱ ተገልጻ ከተመለከትን የየሣምንቶቹን ስንፈትሽ ደግሞ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም፡፡ ምናልባትም በፕሬስ ድርጅትና በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ተሰርቶ ከቀረበው የጥናት መደምደሚያ በላይ የሆኑ ፀረ ልማታዊና ፀረ ዴሞክራሲያዊ የሆኑ ህገ ወጥ ዘገባዎችን መፅሄቷ በነፃ ፕሬስ ስም እያንሸራሸረች ‹‹የፅንፈኛ ፖለቲካውን ስብስብ እንደምትደግፍ›› እንደርስባታለን የሚል እምነት ይኖረኛል፡፡

ሰሞንኛውና ባለጉዳይ የሆኑትን ጨምሮ በሌሎችም የፕሬስ ውጤቶች ዘመቻ የተከፈተበት ጥናት አዲስ ጉዳይን በተመለከተ መደምደሚያው ትክክል እንደሆነ ከላይ ያቀረብኩት ማሣያ ለብቻው በቂ ቢሆንም አንባቢያንም የራሳቸውን ፍተሻና ምዘና በማድግ ከብዥታ ይጠሩ ዘንድና የግል መደምደሚያዬንም ለማጠንከር አንድ መርቄ ወደ ሌላው መፅሄትና ማሳያዬ ብሻገር ተገቢና ምክንያታዊ ያደርገኛል፡፡

ቀደም ያለው ማሣያዬ የመስከረም 2006 ህትመት ነበር፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ሰሞንኛው ጥናትም አይቶት እንደሚሆን ይገመታል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ጥናቱ ካካተታቸው የሦስት ወራት ህትመቶች በኋላ ያለውን የታህሳስ ወር ህትመት ማየት ፍተሻዬን ሚዛናዊ ያደርገዋልና ቅፅ 8 ቁጥር 195 ታህሳስ 2006ን የአዲስ ጉዳይ ዘገባዎች እንዲህ በአዲስ መስመር እንመለከታለን፡፡

የኔልሰን ማንዴላን የቀብር ሥነ ሥርዓት መሠረት በማድረግ በ‹‹ማንን እንማ›› የአዲስ ጉዳይ ገፅ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ክብራቸውን በሚነካና የግል ስብዕናቸውን በሚያንቋሽሽ መንገድ በመፅሄቷ ተወርፈዋል፡፡ በዚያውም የዚህ ገፅ አባሪ በሆነው ‹‹ሃያ ሰባት ዓመታት ያስፈልገን ይሆን›› በሚል በቀረበው ፅሁፍ ህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን መሠረት በማድረግ 27 ዓመታት ከመቆየት በአቋራጭና በኃይል ሥርዓቱን መገልበጥ ተገቢ እንደሆነ የሚያመላክት አንድምታ ያለውን ፅሁፍ አንብበናል፡፡

አሁንም ወደ ውስጥ ስንዘልቅ ‹‹የታፈኑ እውነቶች›› በተባለው የመፅሄቷ አምድ የቀረበው ፅሁፍ በእስልምና ኃይማኖት ሽፋን በሽብር ተግባር ላይ ተሰማርተው የነበሩ ተጠርጣሪ

እሥረኞች ፍትህ እንዳጡና ነፃ መሆናቸውን የሚሰብክ የፍርድ ቤቶች ነፃነት ላይ ህዝቡ እምነት እንዲያጣ የሚጋብዝ  ትርክት መነበቡም እውነትና የቅርብ ጊዜ ዘገባ ነው፡፡

‹‹ንዳው በለው ላሙን አቧራው ይነሳ›› በሚል በዚህችው መፅሄት የፖለቲካ አምድ ላይ የቀረበው ፅሁፍ ደግሞ የገዢ ሥርዓቱ አመራሮች ‹‹እውቀት አልባ›› ናቸው ሲል በጅምላ የሚፈርጅ ንግግራቸውንም ‹‹የእንጦጦ ካህን ቢቀድስ በዓመት እሱም ሬት ሬት›› በሚልና በወቅታዊ ጉዳይ ላይ የሚያደርጉትን ንግግርም ‹‹ቆሮቆንዳ›› በማለት የሚዘልፍ ነው፡፡

ታሳቢ ባለሥልጣናትንም ‹‹ልፍስፍሶችና እረኞች›› በማለት በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትና በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ጥናት መመዘኛ የሰፈሩ ነጥቦችንና ጥናቱም በውጤቱ ከሰጠው ድምዳሜ በላይ የሆነውን ፅንፈኝነት መፅሄቷ በተግባር አረጋግጣልናለች፡፡

ወደ ኋላ የምንመለስበት የጋዜጠኝነት መርሆችና የጋዜጠኝነትንና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ድንበር የተመለከተ ትርክት ከግምት ውስጥ ከተን አዲስ ጉዳይን በዚሁ ዓመት ጥቅምት ወር ላይ ወደ ኋላ ተመልሰን ስንመለከት በሙስና እና በፀረ ሙስና ትግሉ ላይ ያቀረበቻቸውን ሂሶች እናገኛለን፡፡

ሂሶቹና ትችቶቹ በጋዜጠኝነት ሚዛን ተገቢ ቢመስሉም ከተሰጠው ሂስ በስተጀርባ እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን የባለሥልጣናቱን ሀብት ለምን ይፋ ማድረግ ፈራ? በሚል ለቀረበው ትችት ‹‹ሙሰኞች›› እንደሆኑ በዘወርዋራ ለማመላከትና የፈራበትን ምክንያትም (ፈርቶ ከሆነ) በትችቱ ከመዘርዝር ይልቅ ሙሰኞቹ ቱባዎቹ ናቸው የሚል ትርጉም የያዘ ፎቶ ግራፍ በፊት ገፁ አውጥቷል፡፡

እንኳንስ ሙሰኛ እንደሆኑ በፍርድ ቤት ሊረጋገጥ ቀርቶ በተጠርጣሪነት ያልተያዙ ባለሥልጣናትን  በመዳፈር ህዝቡ በሥርዓቱ ላይ እምነት እንዲያጣ የሚያደርግ ከጋዜጠኛነት ሙያ ውጪ በሆነና ምንም እንኳን ይህም ህገ ወጥ ቢሆን የፅንፈኛ ፖለቲካ መንደርተኞች መንገድን በተግባር አሳይታናለች፡፡ ፍተሻ ፋክታችንን ከፋታ በኋላ በክፍል ሁለት እንቀጥላለን።